## መ. አቶ ታምራት ላይኔ

"ትሻልን ወስጄ ትብስን አመጣሁ" እንዲሉ፥ ከጣሊያንና ከደርግ የከፋ ያገርና የቤተ ክርስቲያን ጠላት እንደ አቶ ታምራት ላይኔ ያለውን አገራችን አፈራች።

አቶ ታምራትን ከጣሊያን የከፋ የሚአደርጋቸው፥ ጣሊያን የአብያተ ክርስቲያናትን ሕንጻ እያቃጠለ ካህናት እየገደለ የማይፈልጋቸውን እያስወገደ ለራሱ ፖለቲካ የሚስማሙትን እየሰየመ ሕዝቡን እየፈጀ ድንበር እያፋለሰ ቢገባ ማንኛውም ወራሪ በወረረው አገር ላይ ያደረገው ስለሆነ አያስደንቅም። ያቶ ታምራት ላይኔን ሁኔታ ልዩና የከፋ የሚአደርገው ግን፥ በኢትዮጵያ ተወልደው አድገው የገዛ አገራቸውን፥ ድንበራቸውን እያፈረሱ የሕዝባቸውን ደም እያፈሰሱ ቤተ ክርስቲያንን እያተራመሱ የገቡ በመሆናቸው ነው። አሁንም ቢሆን የቀረውን ዘመናቸውን የሚጨርሱበት የሚሸፍናቸው ጫካ የሚፈልጉ እንጂ በክርስትና መንገድ ቆመዋል ለማለት አያስደፍርም። አቶ ታምራት ላይኔ እውነት ዛሬ እነደሚሉት ኢየሱስ ቢአነጋግራቸው ኖሮ፥ መጀመሪያ ለሰይጣን መሳሪያ ሆነው የሰሩትን ስሕተት እንዲመለከቱ ባደረጋቸው ነበር።

አቶ ታምራት አሁን እሳቸው እንደሚሉት በእርግጥ ኢየሱስ ቢገለጥላቸውማ ኑሮ፥ መጀመሪያ እንደ ኢየሱስ መንገድ ጠራጊ በረሽኛው መጥምቁ ዮሐንስ "መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል"(ማቴ ፫:፲) እያሉ ከእስር ቤት በወጡ ነበር። እኛም የቆዩባትን እስር ቤት ዮሐንስ የኖረበትን ገዳም ባስታወሰችን ነበር። በቆዩበት ቦታ እውነት ክርስቶስ ገልጦላቸው ቢሆን ኖሮ፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን አፍርሰው አቡነ ጳውሎስን ያህል መርግ ደንጋይ የጫኑበትን ፵ ሚሊዮኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሐዶ ሕዝበ ክርስቲያንን መጀመሪያ ይቅርታ በጠየቁ ነበር። እንደ እናቱ እንደ እመቤታች ቅድስት ድንግል ማርያምም "ትቢተኞች ሁሉ ትበተናላችሁ" (ሉቃ ፩:፶፩) እያሉ እርስ በርስ የተካካበውንም ሐሰተኛ ሁሉ እያጋለጡ በጮሁ ነበር። እንደ ኢየሱስም "ድንጋይ በድንጋይ ላይ የተካበ ሳይፈርስ አይቀርም"ና "ምልክቱን አስተውሉ!" የሚለውን ለዘላቂው መፍትሔ የሚበጀውን እየጮኹ በመጡ ነበር። እውነት ኢየሱስን ቢከተሉ ኖሮ "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት" ብሎ ጅራፍ ይዞ

እንደተኮነ፣ እሳቸውም ከሐዲዎች ጳጳሳትን በመጠቀም በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ እራሳቸው ያስቀመጧቸውን አቡነ ጳውሎስን የእውነት ሰው የተዋሕዶው ካህን መለኮት ምስክር መሆን የማይችሉ ነጋዴ ነዎት፥ የተቀደሰውን መንበር ይልቀቁ! እያሉ በጩሁ ነበር። የሰይጣን መጠቀሚያ በነበርኩበት ወቅት አቡነ መርቆርዮስን እንድታወርዱ አንድ ባንድ እየጠራሁ ስነግራችሁ፥ እሺ ብላችሁ በኔ ትዛዝ መሠረት የእግዚአብሔርን ቤት ያረከሳችሁና ፓትርያርካችሁን የካዳችሁ ጳጳሳትም ሁሉ፥ ከእኔ የማትሻሉ፥ እንደውም የባሳችሁ ዓለማውያን ለሹመትና ለሽልማት ያበዳችሁ ስለሆናችሁ አሁን ታዙብኛችሁ። "የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ ስታዩ ተጠንቀቁ" ስለሚል፥ የጵጵስና ማዕረጋችሁን ቶሎ እያደረጋችሁ ከጵጵስናው ቦታ ተወገዱ፥ ስለሰራችሁትም በደል ከልብ ንስሐ ግቡ! ቢሉ ኖሮ የበደሉትን ሕዝበ ክርስቲያን በካሱ ነበር።

እውነተኛውን የቅድስት ድንግል ማርያምን ልጅ ኢየሱስን የተቀበሉ ናቸው ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ብቻ አይደለም በዓለም ዙሪያ ያለው ሁሉ ክርስቲያን በተቀበላቸው፥ የዘመናችን ጳውሎስም በተባሉ ነበር። በዚህ ፍካሬ እራሳቸውን ለኢትዮጵያ ከመግለጽ ይልቅ በሕዝቡ ላይ የሚፈጸምበትን መከራ የቀሎ ተማሪ አኩፋዳ በማድረግ አንገታቸው ላይ አጥልቀው ለራሳቸው መተዳደሪያ ከምዕራቡ ዓለም ቀፈፋቸውን ለመጀመር አቀራረባቸውንና ትጥቃቸውን ለውጠው ወደመከረኛው ሕዝብ ብቅ አሉ። የሚያስደንቀው ነገር፥ ብርቱካን ከቀለጠው ዓለም ካሜሪካ "ከአፏ ለወጣው ቃሏ ዓለምን መንና ልታሰር እያለች ወደ እስር ቤት ስትገባ፥ የኃጥአን መፈክር እንደ ፋሽን የተያዘበት ዘመን ሆነና አቶ ታምራት ከእኛ መነኮሳትና ጳጳሳት ለየት ባለ ዘዴ ወደ አሜሪካ ገሠገሡ። "በስሜ ይመጣሉ" የሚለውን ፍካሬ ኢየሱስ ይፈጸሙ ዘንድ ራሳቸውን በስሙ ሰውረው ከዝቃጭ ሞራላቸው በፈለቀው የእንባ ቅራሪ ሊያበሰብሱን ሞከሩ።

"የእግዚአብሔር መንፈስ የሚአርፍባቸው ሰዎች ስለ እውነት ስለ እምነት ስለ ሕዝብ ሲሉ ቃሌን አለውጥም፥ ወይም ሃይማኖቴን አለውጥም ብለው በሚካፈሉት መከራ እንጅ እንደ አቶ ታምራት ላይኔ የበዘበዙትን ሐብት ከጓደኖቻቸው ጋር ሲዘርፉ በፈጸሙት ግጭት ተፈርዶባቸው በመታሰራቸው አይደለም። የክርስትናችን ሥርአት "ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል" (፩ኛ ጴጥ ፬:፲፭) ነው የሚለው። ክርስትና አቶ ታምራትን ስለመሳሰሉት ሰዎች እየደጋገመ የሚናገረው "በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገስ ምሥጋና ይገባዋል። ኃጢአት እያደረጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሱ ምን ክብር አላችሁ? (፩ኛ ጴጥ ፪:፲፱-፳) እያለ ነው። አቶ ታምራት ላይኔ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን አፍርሰው አቡነ ጳውሎስን ከ፵ ሚሊዮን በላይ በሆነው ሕዝበ ክርስቲያን ላይ አሽከመው ንስሐ ሳይገቡ ሕዝቡን እያስቀጠቀጡ ክርስቶስየ የሚሉብት ቦታ እውነት የኢየሱስ ቦታ ከሆነ በዚያ የሚሰበሰቡ ሁሉ ወገኖች "የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ ስታዩ ተጠንቀቁ"(፲፭) የሚለውን የኢየሱስ ፍካሬ ላስስባቸው እወዳለሁ።